# *አንድነት ፓርቲ አመራር አባላት ለሥልጠና ወደ ደብረዘይት አመሩ፤ ከምርጫ ቦርድ ለቀረበላቸው ጥያቄም መልስ ሰጡ::*

## *የነኢንጅነር ሃይሉ ሻውል፤ ክስ ውድቅ ተደረገ::*

የአንድነት አመራሮች ለሶስት ቀናት ሥልጠና ወደ ደብረ ዘይት የሥራ አመራር ኢኒስቲትዩት አመሩ:: የፓረቲውን ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ያሳድጋል፣የአመራሮቹን ልዩነቶችን በሰለጠነ መንገድ አቻችሎ የመሄድን ብቃት ያበለፅጋል የተባለለትን ሥልጣ በዛሬው እለት ለመጀመር ውደ ደብረዘይት ያቀኑት 16 የሥራ አስፈፃሚ አባላት ናቸው::

ዛሬ የሚጀመረው ሥልጠን ፓርቲው አሻም በሚል መጠሪያ በተከታታይ ለማካሄድ ያቀደው የአቅም ግንባታ የመጀመሪያ ክፍል መሆኑን ከፓርቲው ያገኘነው መረጃ ያመለክታል:: ከዛሬ ጀምሮ ለሶስት ቀናት የማካሄደው ስልጠና በሶስት የተለያዩ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር መሆኑን ባለፈው መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን የአመራር አባላቱ ስልጠናውን ሲጨርሱ እርስ በርሳቸው በሚገባ ይተዋወቃሉ: ፓርቲው ህዝብ የሚጠብቅበትን ተግባር በሚገባ ለመወጣት የሚያስችለውን አስራር ይዞ ይመለሳል የሚል ግምት እንዳላቸው የስልጠናው አስተባባሪ አቶ አክሊሉ ግርግሬ ገልፀዋል::

በተጨማሪም ፓረቲው ጠቅላላ ጉባኤውን አካሂዶ፣ የመመስረቻ ሂደቱን አጠናቆ ለምርጫ ቦርድ አስገብቶና የእውቅና ሰርተፊኬቱን በመጠባባቅ ላይ እያለ የምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ሰነዱን መርምሮ የተለያዩ ችግሮችን አግኝቻለሁ፣ የፓርቲው ስም ሲያጥር የሰውን ስም ይመስላል በማለት ሰነዱ ላይ ማብራሪያ መጠየቁ ይታወሳል:: የፓርቲው አመራር አባላትም በጉዳዩ ላይ ከጽ/ቤጹ ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ሰነዱን በማስተካከል ለቦርዱ አስገብተዋል:: በስሙ ላይ የተነሳው ጥያቄ አግባብ እንዳልሆነና የሰው ስምና የፓረቲ ስም የተለያየ መሆኑን በማመልከት ጽ/ቤቱ ሰነዱን ለቦርዱ በማቅረብ ውሳኔ እንዲያሰጥ ጠይቋል::

በተያያዘ ዜና ምርጫ ቦርድ ስምና አርማችንን ለሌላ አሳልፎ ሰጥቶብናል፣ሊመለስልን ይገባል ሲሉ ምርጫ ቦርድን የከሰሱት እነ ኢ/ር ኃይሉ ሻውል ክሳቸው ውድቅ ተደረገ:: ስምና አርማ ቀይረው ለመንቀሳቀስ መወሰናቸውን አስታውቀዋል::

የቅንጅት ለአንድነት ለዴሞክራሲ ስያሜና አርማ አላግባብ ለሌላ ተሰጥቶብናል በማለት ምርጫ ቦርድን በፍርድ ቤት ሲሞግቱ የነበሩት እነ ኢ/ር ኃይሉ ከሚያዝያ ወር ጀምሮ ያደረጉት ክርክር ውድቅ ተደርጓል:: የፌደራሉ ከፍተኛ ፍረድ ቤት 9ኛው የፍታብሄር ችሎት ከእንግዲህ በስያሜውም ሆነ በአርማው መጠቀም አትችሉም ሲል ውሳኔውን አሳልፏ::

ከውሳኔው በኋላ የእነ ኢ/ር ኃይሉ ብድን ባወጣው መግለጫ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ በሚለው ስያሜ ለመጠቀም እንድንችል ከእስር በተፈታንበት ወቅት ቃል ተገብቶልን ነበር:: ሆኖም ትግሉ ውጤታማ የሚሆነው በስም ሳይሆን በህዝብ ትግል በመሆኑ ስማችንን እና አርማችንን በመቀየር ለመታገል ወስነናል ብለዋል::